**ግጥሞች ውበትን እና እውነትን**[1] ይገልጻሉ፤ የመንፈስን አምድ ይገነባሉ፡፡ የፍልስፍናን መሰረት ይሸከማሉ፡፡ የውንዥብርን የመወላወልን ኣጥር ይንዱሉ፡፡ ግጥሞቼ ከሞላ ጎደል ነጻነትን የሚሰብኩ የንግግር ስልቶች ናቸው፡፡ ይሕች ምድር ነጻነትን በመንፈግ የሚቻላት የለም!!

የንግግር ስልቶች ዝርው/ተራ/ ንግግር፣ ዘይቤ እና ቅኔ ሊሆኑ እንደሚሉ ባለሙያዎች ይጠቅሳሉ፡፡ **ንጉሤ ነገዎ ደጋጋ** በ1983 ባሳተመው ***የቅኔ ሐተታ*** ውስጥ በሰፊው የምንመለከተው ይሕንን ነው፡፡ ተራ ንግግር ማንኛውም ሰው በግልጽ ሐሳቡን በቀላሉ የሚያስተላልፍበት የአነጋገር ስልት ሲሆን፤ ዘይቤ ደግሞ 15 በሚደርሱ አይነቶች ለአብነት ቀርበዋል፡፡[2]

ሶስተኛው አናገር ስልት ቅኔ ነው፡፡ ቅኔ አንድ ቃል በሚሰጠው ቀጥተኛ ትርጉም ብቻ ሳይገታ ወይም ሳይወሰን አስመስለን ጥልቅ የሆነ የተደበቀ ሚስጥርን አጉልተን የምናይበት የምንገልጽት ዘዴ ወይም የአነጋገር ስልት ነው፡፡ የቅኔን ጥቅም ***ደማሙ ብዕረኛ*** መንግስቱ ለማ ግለ ታሪክ ላይ በጥልቀት እናነባለን፡፡ በአእምሮ ጉልበት እየበሰሉ ማደግ ሲቀርብን፤ ቅኔ እየጠፋ የመሄዱ ምልክት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ በአእምሮ መበልጸግ ሲጠፋ አገር የመጥፋቷ መጀመሪያም ነው፡፡ የዚህ ግጥም መድብል ስንኞች ቅኔ ናቸው ባይባሉም፤ ተራ ግጥም ሊሰኙ የሚችሉ የግጥም አይነቶችን ያካተተ መድብል ነው– ሥለ ነጻነት እና አገርን ስለማዳን ግን መታተኑን አያቋርጥም፡፡ **ይስማዕከ ወርቁም** ለጨረቃ ከምትገጥም መሬት ላይ ለወደቀው ወንድምህ አስብ ባለው መሠረት አብዛኞች ግጥሞች የምድርን ነጻነት ያስሳሉ..

ገጣሚና ባለቅኔ በእውቀቱ ስዩም ግጥምን ***ያልተንዛዛ ልቅሶ፣ ያልቆረፈደ ተረብ፣ ያልተዝረከረከ ፍልስፍና መኾኑን እናምናለን***[3] ሲል የገለጸውን እናስታውሳለን፡፡

ግጥም መገለጥ እንደሆነ ያሳመነኝ ይህ ባለቅኔ፤ <<ለገጣሚው የተሰጠ መክሊት>> እንደ ኾነም ሲያምን፤ ገጣሚው ብቻውን የሚደብቀው ነገር (ዲናር) እንዳይሆን እታገላለሁ፡፡ ግጥሞቼ የቅብጸተ ተስፋን /Pessimisim/ ሕልም እንዳያወርሱን እንፈትሻለን ፤ የመወላወልን ንፋስ እንዳያዘንቡም እንማጸናለን፡፡ እንወያያለን፡፡ እንቃወማለን፡፡ ብቻውን ኾኖ መክሊቱን የሚቀብር፤ ሆን ብሎም ለልቡና ዥዋዥዌን ከሚፈጥር ፤ <u>**ጽልመትን ከሚያሰምር ባለቅኔ**</u> ይሰውረን እላለሁ!

"አሌክስ አብርሃም" ግጥም ለሚገጥሙ በሚለው አርዕስት ስንኞቹ ውስጥ እንዲህ ይዘክረናል!!

***ግጥም የሚገጥሙ…***

---

[1] ዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ፡ ‹‹የተስፋ ክትባት›› የግጥም መድብል 2008 ዓ.ም -መግቢያ
[2] ተለዋጭ ዘይቤ፣ ተነጻጻሪ ዘይቤ፣ ግነት ዘይቤ፣ ምጸት ዘይቤ፣ ጽላሎት ዘይቤ፣ ሰውኛ ዘይቤ፣ ምስያ ዘይቤ፣ ተምሳሌት ዘይቤ፣ አፍላ ዘይቤ፣ የቁልቁል ዘይቤ፣ አፍራሽ ዘይቤ፣ ተሳልቆ ዘይቤ፣ አሽሙር ዘይቤ፣ ገድሎ ማዳን ዘይቤ፣ አድኖ መግደል ዘይቤ ናቸው፡፡
[3] በዕውቀቱ ስዩም ‹‹ኗሪ አልባ ጎጆዎች›› (ስብስብ ግጥሞች 2001 ዓ.ም)

*የዓለም እንቆቅልንቆ ነፍስ የሚያስገባ*

*ስንጥቅ ልባቸውን በፍቅር ያክሙ ፣*

*በጨቀዬ ምድር ድርቅ ላይ ይቁሙ ፣*

*የባህር ልጅ ሆነው ጠብታ ይጠሙ…ሲል*[4] ገጣሚውን ይገስጻል ፡ ፡ **<u>ገሳጭ ባለቅኔ</u>** አያሳጣንም እንላለን!!

በዚህ መድብል ውስጥ የተለያዩ ገጣሚያን ሐሳባቸውን እና ዘይቤያቸውን ማሳረፋቸው አልቀረም ፡ ፡ ለአንድ ሰሞን በተከታታይ የማነባቸው የግጥም ስራዎች የግጥሞቼን ዜማና የስንኝ አደራደር ይቃኙታል ፡ ፡ ሌላኛው ደግሞ በሌላው ቀን ይከተላል ፡ ፡

እንደ ጉባኤ ቃና ያሉ ሁለት ዘለላዎችን ያዘሉ "ነጻ" ግጥሞች እኩል ገጽ ተሰጥቷቸው ነጻነታቸውን አውጀዋል ፡ ፡ የግጥሞቼ አብዛኛው ሽክማቸው <<ነጻነት>> ነው ብያለሁ ፡ ፡ "አርዑት" እንዲል የመድብሉ ስያሜ ፡ ፡

ሆኖም ግን ነጻነት ባርነት ነው!

የሰው ልጅ በቃላት ተታሎ ፤ በፍላጎት ተጠርንፎ ፤ እናሳካልሃለን በሚሉት የኀይል ባለንጣዎች ነጻነቱን እንደ ስጋ ተከታይ ውሻ ሲሮጥ ፣ ሲሮጥ.. ሲከተል ይኼው ሽህ ዘመናት አለፉበት ፡ ፡ የነገሥታት ጉልቻዎች ተለዋወጡ ፡ ፡ "ዲሞክራሲ ፣ እኩልነት ፣ ፍትህ ፣ አንድነት" በሚባሉ "ተስፋዎች" ስንቱ ከስንቱ ተጨራረሰ? ራስን በራስ የመወሰን ፣ ሰብአዊ መብቶች ፣ ወንድማማችነት ፣ የተባበሩት መንግሥታት… ወዘተ አስተሳሰብ "ቃሎች" ናቸው ፡ ፡ የሚሉን ደግሞ አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ ፡ ፡ በ "አልቦ ዘመድ" አንጓር ሥራቸው በገጽ 30 ዘርዝረው ሲገልጹ እናያለን ፡ ፡ ነጻነት ባርነት ሲሆን!?

ሕገ አራዊትነት እስከሠለጠነብን ፣ የሠው ልጅ በመሣሪያ ፣ በጫራ ፣ በብረት እና በጠበንጃ ማሰብ እስከቀጠለ ድረስ አዎን <<ነጻነት ባርነት>> ነው ፡ ፡ መስፍን ወልደማርያም አጥብቆ የሚመኙው ይሕንን ነበር!! ከሕገ አራዊትነት ተላቅቆ በሕገ ኀልዮት ሜዳ በነጻነት መሠለፍ!! ይሕች ምድር ግን ይሕንን ለማሳየት የታደለች አትመስልም ፡ ፡ የመኖርም የመሞትም አላማ ግን ይሕንን መስበክ እና ለማሳካት መታገል ነው ፤ ልሳን እስኪከስም ይሕንን መዘመር ነው ፡ ፡ በሥነ-ጽሑፍ ጋሻ ፣ በጥበብ ሰይፍ ፡ ፡ ግጥሞቹም ለነጻ-ነት መዝሙር ሆነው ይቀጥላሉ- ተፈጥሮአዊ ሰብዓዊም ነው! አራዊቶች አይገጥሙም ፣ አዕዋፋት ይዘምራሉ ከእነርሱ ዜማ እየቀዳን ስንኞችን እናሰናዳለን- አዕዋፋት በማለዳ የነጻነት ዜማን ይሰብካሉ- የሚያዳምጣቸው የታደለው ነው!

ጸሐፊው ፡ ፡

---

[4] አሌክስ አብርሃም (የብዕር ስም)፡ እናት ፍቅር ሐገር፡ 2007 ዓ.ም

## ፍቅር አርዑት ነው

እኛን እያኖረ እሱ የሚሞተው

እኛኑ በመቅተል ራሱን ‘ሚያኖረው

ፍቅር *አርዑት*[5] ነው ፡ ፡

የሰው ልጅ በሬ ነው ቀንበር የበዛበት

ኣንዱ ሲለዝበት ሌላው ‘ሚያይልበት ፡ ፡

ሕግ ኣምላክ ፈጣሪ

ያገዛዝ ልቡና የምድር ነጋሪ

ኣማልክት በሰማይ በምድር ቢኖሩ

በሰው ልጅ ጫንቃ ላይ የሚመላለሱ

ፍቅር አርዑት ነው ሚነዳ በነርሱ

ተነጺው “ሰው” ሆኗል ተሸካሚው እሱ ፡ ፡

---

[5] አርዑት፡- *መጥመጃ፣ መጠመጃ፤ ቀንበር፤ ሕግ፣ ሥርዓት፤ አገዛዝ፤ እግር ብረት፡፡ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ገጽ 834/5፡፡*

# የእንባቿን ምስጢር!!

የፊቴ ፀዳል ይከስማል
የልቤ ብርሃን ይቀልጣል፡ ፡
የፍቅሬ ትውፊት ይከሽፋል ÷ የነጸነት መዝሙሬ ይሰንፋል!
ያልተረዳሺኝ ʿለት ያላልኩት ሲገባሽ
ያልኩት ካልተሰማሽ ልሳኔም ካልገዛሽ
የፊቴ ፀዳል ይከስማል...
የልቤ ብርሃን ይነጥፋል፡ ፡
-/-
የዘመርኩልሽ ካላጸናሽ የሞትኩልሽ ካላዳነሽ ፤
የወደቅሁልሽ ካላነሳሽ የወረድኩልሽ ካላኀነሽ
የፊቴ ፀዳል ይከስማል
የልቤ ብርሃን ይነጥፋል
ያካሌ ደምም ይሞቃል፡ ፡

ጠኬቴ ካልሆነብሽ ÷ ሕመሜ ካልፈወሰሽ
የስጋ ስቤ ይቀልጣል
የነፍሴ ሐሞት ይፈስሣል...፡ -
የልቤ ጊዳው ይበርዳል...!!
ያኔ
እንባዬም በሆዴ ይዘንባል!!

# የጤዛዋ[6] ተስፋ-1

የጤዛዋ ተስፋ መክሰም ነው ፤
ፍካት ፤ ለቅጽበት
መብሯት ፤ ለመጥፋት፡ ፡
የጤዛዋ ምኞት መክሰም ነው
መድመቅ ለወረት ፤
ማጌጥ ለድይኘ ፤ መኘጸት ለጽልመት፡ ፡

[6] “ጤዛዊነት”ን ልብ ይሏል

# አገርና ሽንት ቤት

ሰው ያለው አገር ነው ፤
ሽንት ቤትም እንዲው
ሰው አለ እያልን የምንመልሳቸው
ሁለቱም ያው ናቸው ፤ ለሰው ልጆች ናቸው ፡ ፡
ጽዳት ንጹ–እና ለውጥም የሚያሻቸው
ክትትል ቁጥጥር የሚያስፈልጋቸው
አገርም ሽንት ቤት ሁልጊዜ ያው ናቸው!